# መቅድም ።

ሼክስፒር ፡ ከተወለደ ፡ ዘንድሮ ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ሞላው ። ድርሰቶቹ ፡ ከጻፋቸው ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ናቸው ። ወደፊት ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መወደድን ፡ እየጨመሩ ፡ እንደሚሄዱ ፡ በታላላቅ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሊቃውንት ፡ ይገመታል ።

ዕውቀት ፡ የደረሰው ፡ ዓለም ፡ የዚህን ፡ የደራሲ ፡ ጽሑፎች ፡ ሲያነብ ፡ ከ፫፻፶ ፡ ዓመት ፡ በልጦታል ። የሚያነባቸውም ፡ በተጻፈበት ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ወይም ፡ በሚናገረው ፡ በትውልድ ፡ ቋንቋው ፡ ነው ። በማንኛውም ፡ አገር ፡ ከውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ይልቅ ፡ የራሳቸውን ፡ ቋንቋ ፡ የሚያውቁ ፡ እጅግ ፡ ስለሚበልጡ ፡ እየተተረጐመላቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በናት ፡ ቋንቋቸው ፡ እንዲያነቡ ፡ ዕድል ፡ አግኝተዋል ። ይህን ፡ ዕድል ፡ የሰጣቸውን ፡ ተርጋሚዎች ፡ ስም ፡ ከታላቁ ፡ ደራሲ ፡ ስም ፡ ጋራ ፡ ሲጠሩ ፡ ይኖራሉ ። ንባብ ፡ የሚያፈቅሩ ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ ጽሑፎች ፡ በአማርኛ ፡ ለሚተረጉምላቸው ፡ ሰው ፡ የልብ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይኖርባቸዋል ። እንዲያውም ፡ ጽሑፎቹ ፡ እንደ ፡ ተጻፉ ፡ ዕውቀት ፡ የደረሰው ፡ ዓለም ፡ ሲያነባቸው ፡ እኛ ፡ የሱን ፡ ጽሑፎች ፡ ከማንበብ ፡ ከ፫፻፶ ፡ ዘመን ፡ ይበልጥ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተናል ። አሁንም ፡ እንደ ፡ አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ያሉ ፡ ተርጋሚዎችና ፡ ደራሲዎች ፡ ባይኖሩን ፡ ዘመኑ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ቢውልብን ፡ ሊያድርብን ፡ ኑሯል ።

የአንድ ፡ ቋንቋ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያድገው ፡ የሚስፋፋው ፡ ድርሰቶችን በመድረስና ፡ ድርሰቶችን ፡ በመተርጐም ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ የማይተናነሱ ፡ ችሎታዎች ፡ ሲሆኑ ፡ አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ይህና ፡ ያለፉት ፡ ጽሑፎቹ ፡ እንደሚያመለክቱት ፡ ሁለቱንም ፡ ስጦታዎች ፡ አዳምሮ ፡ የያዘ ፡ ወጣት ፡ ደራሲ ፡ ነው ። የአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ በተለየ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ ያሉትን ፡ ደራሲዎች ፡ የሥራ ፡ ቋንቋ ፡ ያረጉት ፡ ዘንድ ፡ መብራት ፡ ይዞ ፡ ይፈልጋቸዋል ።

አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ የሼክስፒር ፡ ድርሰቶችን ፡ ሲተረጉም ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ኦቴሎን ፡ ከተቀዳሚዎቹ ፡ ውስጥ ፡ እንዳደረገው ፡ አልነገረኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ የወገናችን ፡ የቤት ፡ ሰብ ፡ ኑሮ ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ ስለሚፈታ ፡ ምክሩን ፡ በሼክስፒር ፡ ስም ፡ ሊያበረክት ፡ የፈለገ ፡ ይመስለኛል ።

አቶ ፡ ጸጋዬ ፡ እንደማውቀው ፡ ዝምተኛ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጻሕፍቶቹ ፡ ያወራልናል ። በሚያቀርባቸውም ፡ ተውኔቶች ፡ ያጫውተናል ። የረጋ ፡ ውሀ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፡ እንደሚባለው ፤ የረጋ ፡ የተደላደለ ፡ አእምሮው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ሐሳቦችን ፡ ይዟል ።

ዶክተር ፡ ጌታቸው ፡ ኃይሌ ፡

ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ።

Scanned by CamScanner

